# 19ኛው የሜጀር ጄኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር

# ህግና ደንብ

## የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

ታህሳስ 08 ቀን 2010 ዓ.ም.

ድሬደዋ

# 19ኛው የሜጀር ጀኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር ሕግና ደንብ መመሪያ

## ዓላማ

የሜጀር ጀኔራል ኃየሎም አርአያ ተጋድሎ ታሪክ በየዓመቱ ለማሰብና ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ክለቦች በ15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር በመካፈል ልምድ እንዲያካብቱ ለማድረግና ተተኪ አትሌቶች ለማፍራት፤ እንዲሁም ለአትሌቶች የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር ዕድል ለመፍጠር ነው፡፡

## *አንቀጽ አንድ*

## *አጠቃላይ የውድድሩ ደንብ*

1. **የውድድሩ መጠሪያ፡-** ይህ ውድድር 19ኛው የሜጀር ጀኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ተብሎ ይጠራል፡፡
2. **ውድድሩን የሚመራው፡-** 19ኛው የሜጀር ጀኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በIAAF ሕግና ደንብ መሠረት ይመራል፡፡
3. **ውድድሩን በበላይነት የሚመራ አካል፡-** 19ኛው የሜጀር ጀኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በበላይነት ይመራል፡፡
4. **የውድድሩ ተሳታፊዎች፡-** በ19ኛው የሜጀር ጀኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦችና የስፖርት ተቋማት ይሳተፋሉ፡፡

## *አንቀጽ ሁለት*

## *የውድድሩ ቀን፣ ቦታና ሰዓት*

19ኛው የሜጀር ጀኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ታህሳስ 08/2010 ዓ.ም. በድሬደዋ ከ/አስተዳደር ከጠዋቱ 1፡00 ሰዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡

## *አንቀጽ ሦስት*

## *የውድድር ርቀት*

19ኛው የሜጀር ጄኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ርቀት 15 ኪ.ሜ. ነው፡፡

## *አንቀጽ አራት*

## *የውድድሩ ካታጎሪ*

1. ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በሁለቱም ፆታ በምድብ አንድ ካታጎሪ እንዲሁም፤
2. ክለቦችና የአትሌቲክስ ተቋማት በሁለቱም ፆታ በምድብ ሁለት ካታጎሪ ተመድበው ይወዳደራሉ፡፡
3. የግል ተወዳዳሪዎች በሁለቱም ፆታ ከብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ቁጥር በመግዛት እና ትክክለኛ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ ይወዳደራሉ፡፡

## *አንቀጽ አምስት*

## *የተወዳዳሪ አትሌቶች እድሜ*

ዕድሜያቸው ቢያንስ ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ አትሌቶች በውድድሩ ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ አትሌቶች በዚህ ውድድር ላይ መሳተፍ አይችሉም፡፡

## *አንቀጽ ስድስት*

## *የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር*

ማንኛውም ተወዳዳሪ አትሌት የመወዳደሪያ ቁጥር ሊኖረው ይገባል፣ ቁጥሩ የሚለጠፈው ግልጽ ሆኖ በሚታይ ቦታ በደረትና በጀርባ ላይ ነው፡፡ ማንኛውም አትሌት የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር ለብሶ መሮጥ አለበት፡፡ የመወዳደሪያ መሮጫ ቁጥር የሌለው አትሌት በውድድሩ ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡

## *አንቀጽ ሰባት*

## *በውድድሩ ስፍራ በሰዓት መገኘት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ ውድድሩ ከመጀመሩ ከ45 ደቂቃ በፊት በውድድሩ ቦታ በመገኘት ለውድድሩ ዝግጁ መሆኑን ለስም ጠሪ ዳኞች ማሳወቅ ይኖርበታል፤ በስም ጥሪ ቦታ ተገኝቶ ስሙን ለስም ጠሪ ዳኞች ያላሳወቀ አትሌት በውድድሩ ላይ መካፈል አይችልም፤ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡

## *አንቀጽ ስምንት*

## *የምዝገባ ጊዜ*

1. 19ኛው የሜጀር ጄኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ምዝገባ ከህዳር 26 እስከ ታህሳስ 02/2010 ዓ.ም. ድረስ ጉርድ ሾላ በሚገኘው የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት የተወዳዳሪዎችን ስም ዝርዝር በመላክ መመዝገብ ያስፈልጋል፡፡
2. በውድድሩ የምዝገባ ገደብ ውስጥ ያልተመዘገበ ክልል/ከተማ አተዳደርና ክለብ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) በመክፈል ታህሳስ 03/2010 ዓ.ም. ብቻ መመዝገብ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ተሳታፊ ክልል/ከተማ አስተዳደርና ክለብ በየፆታው ከሦስት እስከ ስድስት አትሌቶችን ማስመዝገብ ይችላል፡፡

## *አንቀጽ ዘጠኝ*

## *የተወዳዳሪ መታወቂያ*

የክልል/ከተማ አስተዳደር ተወዳዳሪ አትሌቶች በዳኞች ስም ጥሪ ቦታ ማንነታቸውን የሚገልጽ በዘመኑ የታደሰ መታወቂያ እንዲሁም የክለብ ተወዳዳሪዎች የክለባቸውን ቴሴራ እንዲሁም የግል ተወዳዳሪዎች ማንነታቸውን እና ዕድሜያቸውን በትክክል የሚገልፅ መታወቂያው ለስም ጠሪ ዳኞች ማሳየት ይኖርባቸዋል፡፡ ነገር ግን መታወቂያው ስርዝ ድልዝ ካለው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

## *አንቀጽ አስር*

## *ክስና ይግባኝ ስለማቅረብ*

1. የአትሌት ተገቢነት የክስ ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው ውድድሩ ከመጀመሩ ቢያንስ ከ30 ደቂቃ በፊት ነው፡፡
2. የውድድር ውጤቶችን ወይም የውድድር ተግባሩ ሂደትን በተመለከተ የክስ ጥያቄ የሚቀርበው ውጤቱ ይፋ በሆነ በ30 ደቂቃ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡
3. ማንኛውም የክስ ጥያቄ መጀመሪያ የሚቀርበው ለውድድሩ ዳኛ በቃል በአትሌቱ፣ በአሠልጣኙ ወይም በቡድን መሪው አማካይነት ሊሆን ይችላል፡፡ የውድድር ዳኛው ውሳኔ መስጠት ወይም ጉዳዩን ለክስ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. በዳኛው ውሳኔ ያልተስማማ አካል በጽሑፍ ከብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) ጋር ለክስ ሰሚ ኮሚቴ ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ ክሱም በ30 ደቂቃ ጊዜ ውሳኔ ያገኛል፡፡
5. ክሱ በክስ ሰሚ ኮሚቴ ተጣርቶ ተገቢ ክስ ሆኖ ከተገኘ የተያዘው ብር ተመላሽ ሆኖ ክሱ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ክሱ ተቀባይነት ካላገኘ የተያዘው ብር ለፌዴሬሽኑ ገቢ ሆኖ ውሳኔው የፀና ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስራ አንድ*

## *አለባበስ*

ማንኛውም ተወዳዳሪ የክልሉን፣ የከተማ አስተዳደሩን የተቋሙን እና የክለቡን መለያ የሆነውን የስፖርት ትጥቅ ለብሶ ለውድድርም ሆነ ለሽልማት መቅረብ አለበት፡፡ ማልያ ለብሶ ያልቀረበ ተወዳዳሪ መወዳደር አይችልም፤ ተወዳድሮ ቢገኝ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡ አንድ ቡድን አንድ ዓይነት መለያ መልበስ አለበት፡፡ የግል ተወዳዳሪዎች የግላቸውን መለያ መልበስ ይችላሉ፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሁለት*

## *የአትሌቱ/ቷ ጤንነት*

በውድድር ተካፋይ የሚሆኑ አትሌቶች ጤንነታቸው የተሟላ መሆን አለባቸው፡፡ የጤንነት ችግር ያለባቸው አትሌቶች ተወዳድረው ቢገኙና ጉዳት ቢደርስባቸው ተጠያቂ የሚሆነው ክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ፣ ክለቡ እና አትሌቱ ራሱ ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አስራ ሦስት*

## *የሥነ-ሥርዓት ጉድለት*

ማንኛውም ተወዳዳሪ፣ አሰልጣኝ፣ የቡድን መሪ፣ ወጌሻ ወይም ሌሎች የቡድን አባላት ውድድሩ በሚከናወንበት ወቅት የሥነ-ሥርዓት ጉድለት ካሣየና ውድድሩን በሚመሩ ዳኞች ወይም የውድድር አመራሮች ሪፖርት ቀርቦ ጥፋቱ ከተረጋገጠ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተዘጋጀው የአሠልጣኞች፣ አትሌቶችና የክለቦች የሥነ-ምግባር ደንብ አንቀጽ አስር መሠረት ይቀጣል፡፡

## *አንቀጽ አስራ አራት*

## *ሽልማት*

1. ከ1ኛ-3ኛ ለሚወጡ አትሌቶች፣ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ተቋሚትና ክለቦች ተለይተው በየደታቸው የወርቅ፣ የብር እና የነሐስ ሜዳልያ ሽልማት ይሰጣል፡፡
2. በየውድድሩ ከ1ኛ-6ኛ ለሚወጡ አትሌቶች በሁሉም ካታጎሪ የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፡፡
3. የቡድን አሸናፊ ለሚሆኑ ክልሎች ከተማ አስተዳደሮችና ክለቦች ተለይተው በየደታው የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት

## የቡድን ውጤትን በተመለከተ

1. በሁለቱም ካታጎሪ በየፆታቸው ለውድድር ከተመዘገቡት ከስድስት ተወዳዳሪዎች ውስጥ መጀመሪያ ቀድመው የገቡት የሦስቱ አትሌቶች የቡድን ነጥብ ተደምሮ አነስተኛ ነጥብ ያስመዘገበ ቡድን የውድድሩ አሸናፊ ይሆናል፡፡

   **ምሳሌ፡-** ቡድን ሀ 1ኛ፣ 5ኛ፣ 8ኛ ቢወጡ የቡድኑ ውጤት ድምር 14 ነው

   ቡድን ለ 2ኛ፣ 3ኛ እና 6ኛ ቢወጡ የቡድኑ ውጤት ድምር 11 ነው

   በዚህ ድምር ውጤት መሠረት አሸናፊ ቡድን "ለ" ይሆናል፡፡

   ነገር ግን ቡድኖች የውጤት ድምራቸው እኩል ቢሆን መጨረሻ ነጥብ ያስመዘገበ (ዘጊው) አትሌት ማለትም ለአንደኛው የቀረበው የአትሌት ቡድን አሸናፊ ነው፡፡

   **ምሳሌ፡-** ቡድን ሀ 1ኛ፣ 5ኛ እና 8ኛ ቢወጡ የቡድኑ ውጤት ድምር 14 ነው

   ቡድን ለ 2ኛ፣ 3ኛ እና 9ኛ ቢወጡ የቡድኑ ውጤት ድምር 14 ነው

   ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ቡድኖች ነጥባቸው እኩል ቢሆንም ለአንደኛው የቀረበ ዘጊው አትሌት 8ኛ የወጣ የ"ሀ" ቡድን ስለሆነ የ"ሀ" ቡድን አሸናፊ ነው፡፡
2. ከሦስት አትሌቶች በታች ውጤት ያስመዘገቡ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮችና ክለቦች በቡድን ውጤት ደረጃ ባያስመዘግቡም ባላቸው ውጤት አትሌቶቹ በግል ይሸለማሉ፡፡
3. በአንድ የውድድር ካታጎሪ ከሁለት ቡድኖች እና ከሦስት አትሌቶች በታች ከተመዘገቡ ውድድሩ ይሰረዛል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት

## የክልሎችና የከተማ አስተዳደር ቡድኖች ኮታ

1. የትግራይ ክልል 10 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
2. የአማራ ክልል 10 በው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
3. የኦሮሚያ ክልል 10 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
4. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል 10 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
5. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር 10 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
6. የአፋር ክልል 6 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
7. የጋምቤላ ክልል 6 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
8. የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል 6 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
9. የሐረሪ ክልል 6 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
10. የድሬደዋ ከተማ አስተዳድር 6 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤
11. የኢትዮ ሱማሌ ክልል 6 ሰው አሠልጣኝና ቡድን መሪ ጨምሮ፤

## *አንቀጽ አሰራ ሰባት*

## *የአበልና ትራንስፖርት ክፍያ*

የክልል እና የከተማ አስተዳድር ተወዳዳሪዎች በተሰጣቸው ኮታ መሠረት አበልና መጓጓዣ ይከፈላቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ከተሰጠው ኮታ በላይ አትሌት ይዞ የመጣ ክልል/ከተማ አስተዳድር በራሱ የአትሌቶችን ወጪ የሚሸፍን ይሆናል፡፡

## *አንቀጽ አሰራ ስምንት*

## *የቴክኒክ ስብሰባ*

የቴክኒክ ስብሰባ ታህሳስ 07/2010 ዓ.ም. ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ይካሄዳል፡፡ በስብሰባው ላይ የሚገኙ ከየቡድኑ አንድ ቡድን መሪና አንድ አሠልጣኝ ይሆናሉ፡፡

# 19ኛው የሜጀር ጄኔራል ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ. የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ኘሮግራም

ቀን፡- <u>ታህሳስ 08/2010</u>

የውድድሩ ቦታ፡- <u>ድሬደዋ</u>

| ተ.ቁ. | ሰዓት | ክንውን | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|
| 1. | 1፡00 | የውድድሩ ስፍራ ለተመልካቾች ክፍት ይሆናል | በውድድሩ አስተናጋጅ ኮሚቴ |
| 2. | 1፡30 | የክልሎችና የከተማ አስተዳደር እንዲሁም የክለብ ተወዳዳሪዎች ስም ጥሪ ይደረጋል | በስም ጠሪ ዳኞች |
| 3. | 1፡45 | የሴቶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| | 2፡00 | የወንዶች ውድድር ይጀመራል | በአስነሺ ዳኞች |
| 4. | 3፡30 | ለክልልና ከተማ አስተዳደር ተወዳዳሪ አሸናፊ ሴት አትሌቶች የሜዳሊያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፤ | በተጋባዥ እንግዳ |
| 5. | 3፡40 | ለክልልና ከተማ አስተዳደር ተወዳዳሪ አሸናፊ ወንድ አትሌቶች የሜዳልያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፤ | በተጋባዥ እንግዳ |
| 6. | 3፡50 | ለክለብ አሸናፊ ሴት አትሌቶች የሜዳልያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፤ | በተጋባዥ እንግዳ |
| 7. | 4፡00 | ለክለብ አሸናፊ ወንድ አትሌቶች የሜዳልያና የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፤ | በተጋባዥ እንግዳ |
| 8. | 4፡10 | ለክልል/ከተማ አስተዳደር እና ክለቦች አሸናፊዎች የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል | በዕለቱ የክብር እንግዳ |
| 9. | 4፡30 | የውድድሩ ፍፃሜ ይሆናል | |

*የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን*

# የ19ኛው ሜ/ጀ/ኃየሎም አርአያ መታሰቢያ 15 ኪ.ሜ የጐዳና ላይ ሩጫ ውድድር

# የተወዳዳሪዎች መመዝገቢያ

ክልል/ከተማ አስተዳደር/ክለብ/ተቋም ______________________________

| ወንዶች | | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ. | የአትሌቱ ስም | የትውልድ ዘመን |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

| ሴቶች | | |
|---|---|---|
| ተ.ቁ. | የአትሌቷ ስም | የትውልድ ዘመን |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

የቡድን መሪ ስም______________________________________

የአሠልጣኝ ስም______________________________________

ቅጹን የሞላው ሰው ስም______________________________

ኃላፊነት______________________________________

ፊርማ______________________________________

ቀን______________________________________